10/30/25

ውድ ወላጆች እና አሳዳጊዎች፣

የትምህርት ቤት የጤና አገልግሎቶች ፕሮግራምን በተመለከተ ለአሁኑ የ2025-2026 የትምህርት ዘመን ጠቃሚ አዳዲስ መረጃዎችን ለማካፈል እየጻፍን ነው። ከዚህ ዓመት ጀምሮ፣ DC Health ከዚህ ቀደም በድጋፍ ሰጪዎች ይተዳደር ከነበረበት አሠራር ወጥቶ፣ ፕሮግራሙን በራሱ ወደ ሚመራበት ሞዴል ይሸጋገራል። ይህ ለውጥ የተማሪዎችን የጤና አገልግሎቶች ይበልጥ ወጥና ቀጥተኛ በሆነ መልኩ ለመቆጣጠር ይረዳናል። ሁሉም የጤና ክፍል ሰራተኞች አሁን በቀጥታ በDC Health የሚቀጠሩ እና የሚተዳደሩ ይሆናሉ።

**አገልግሎቶች እና ሰዓቶች:-**
የሚከተሉት አገልግሎቶች በትምህርት ቤቱ የጤና ክፍል ውስጥ መሰጠታቸውን ይቀጥላሉ።

- የመጀመሪያ ደረጃ እርዳታ እና የድንገተኛ ጊዜ እንክብካቤ
- የመድሃኒት አስተዳደር (መስጠት)
- የእይታ እና የመስማት ምርመራዎች
- በቴሌፎን የታገዘ የጤና አገልግሎቶች (ቴሌሄልዝ)
- ለግለሰብ የተዘጋጁ የጤና ዕቅዶች
- የእንክብካቤ ማስተባበር
- ክትባቶች

የጤና ክፍሎች በየሳምንቱ ከ20 እስከ 40 ሰዓታት አገልግሎት ይሰጣሉ። አጠቃላይ የጤና ክፍሎች የሥራ ሰዓት ከ8:00am እስከ 4:30pm ነው።

**የሰራተኞች ምደባ:-**
የጤና ክፍል ሰራተኞች በክላስተር ላይ በተመሰረቱ ቡድኖች መስራታቸውን ይቀጥላሉ። ክላስተሮች እርስ በርስ ተቀራርበው የሚገኙ ትምህርት ቤቶችን ያካትታሉ። እያንዳንዱ ክላስተር በተመዘገበ ነርስ እና በነርስ የሥራ ሃላፊ ቁጥጥር ይደረግበታል። በልጅዎ የጤና ክፍል ውስጥ ከሚከተሉት ባለሙያዎች አንዱን ወይም ከዛ በላይ ሊያገኙ ይችላሉ:-

| ሚና | ሃላፊነቶች |
|---|---|
| የተመዘገበ/ች ነርስ (RN) | የመጀመሪያ እርዳታ፣ መድሃኒት መስጠት፣ የድንገተኛ ጊዜ ምላሽ፣ የጤና መዛግብት ግምገማ፣ ክትባቶች፣ የእንክብካቤ ማስተባበር፣ ልዩ እንክብካቤ እና የጤና ዕቅዶችን ማዘጋጀት |
| ፍቃድ ያለው/ያላት የተግባር ነርስ (LPN) | ከRN ጋር ተመሳሳይ ነው፣ ነገር ግን የጤና ዕቅዶችን አያዘጋጁም |
| የጤና ቴክኒሻን | የመጀመሪያ እርዳታ፣ መድኃኒት መስጠት፣ የድንገተኛ ጊዜ ምላሽ፣ መረጃ ማስገባት |

ማሳሰቢያ፡- የሰራተኞች ምደባ ባለፈው የትምህርት ዓመት ከነበረው ጋር ተመሳሳይ እንዲሆን ለማድረግ ብንጥርም፣ በ2025–2026 በልጅዎ ትምህርት ቤት ተመሳሳይ ሰራተኞች እንደሚመደቡ ዋስትና መስጠት አንችልም።

**<u>የትምህርት ቤት የጤና ቅጾች፡-</u>**

ተማሪዎ ተገቢውን እንክብካቤ ማግኘቱን/ማግኘቷን ለማረጋገጥ፣ እባክዎ የሚከተሉትን ቅጾች ሞልተው ለትምህርት ቤትዎ ዋና ቢሮ ያስገቡ፡-

- **ሁሉን-አቀፍ የጤና የምስክር ወረቀት፡-** በየዓመቱ ለትምህርት ቤትዎ መቅረብ ያለበት፣ ከልጅዎ የሕክምና አገልግሎት አቅራቢ የሚሰጥ የጉብኝት ሪፖርት።
- **የትምህርት ቤት ጤና አገልግሎቶች የስምምነት ቅጽ፡-** ልጅዎ መመዝገቡን እና የSHSP አገልግሎቶችን መጠቀም እንደሚችል ያረጋግጣል። ይህ ቅጽ አንድ ጊዜ ብቻ ነው የሚያስፈልገው።
- **የመድኃኒት እና የሕክምና ፈቃድ፡-** ልጅዎ የሚያስፈልጉትን መድሃኒቶች እና ሕክምናዎች ለጤና ክፍሉ ይገልጻል። የመድሃኒት ወይም የመጠን ለውጦች ካሉ፣ አዲስ ቅጽ በሐኪም መሞላቱን እና ለትምህርት ቤትዎ መቅረቡን ያረጋግጡ።
- **የተግባር ዕቅዶች፡-** ልጅዎ አስም፣ አናፍላክሲስ (anaphylaxis - ከባድ የአለርጂ ምላሽ) ወይም የነርቭ መታወክ ካለበት፣ የተግባር ዕቅዱን ወዲያውኑ ማስገባትዎን ያረጋግጡ። የእንክብካቤ ዕቅዳቸው ከተቀየረ አዲስ ቅጽ ማስገባት ይኖርብዎታል።

**ማስታወሻ፡-** እነዚህ የጤና ቅጾች ልጅዎ በትምህርት ቀን ውስጥ ትክክለኛውን እንክብካቤ እንዲያገኝ አስፈላጊ ናቸው። የልጅዎ የሕክምና አገልግሎት አቅራቢ እነዚህን ቅጾች እንዲሞላ ይጠይቁ። የትምህርት ቤቱን የጤና ቅጾች ቅጂ ለማግኘት፣ እባክዎ የትምህርት ቤት የጤና አገልግሎት ፕሮግራም ድረ-ገጽን ይጎብኙ።

ተማሪዎቻችንን ጤናማና ደህንነታቸው የተጠበቀ ለማድረግ ለሚያደርጉት ድጋፍ እና አጋርነት እናመሰግናለን። ጥያቄዎች ካሉዎት፣ እባክዎን ትምህርት ቤትዎን ወይም የትምህርት ቤት የጤና አገልግሎት ፕሮግራምን በቀጥታ በshs.program@dc.gov ያግኙ።

ከሰላምታ ጋር፣
የዲሲ የጤና መምሪያ — የትምህርት ቤት የጤና አገልግሎት ፕሮግራም